# የጉሙዝ ሴት ጩሆት 1

ኡ ኡ ኡ ኡ እረ እርዱኝ መላ መላ ፈልጉ፣

በእኛው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተጎድቻለሁ በእጁጉ፣

ገና በልጅነቴ ጫወታ ተጫውቼ ሳልጨርስ፣

ለጋብቻ በቃች ተባልኩኝ እንጊዳስ፣

ወንድሜ ሊያጋባ ቀየሩኝ ሌላ ሰው!

እደልዋጭ ዕቃ ሰብዕናዬ የሠው!

እኔ ለትዳር ምኑን አውቃዋለሁና፣

ሠውነቴ ለጋ መቼ ደረሰና፡፡

ዓመት ሣይሞላኝ አረገዝኩኝና፣

ተሠቃየሁኝ በጣም ሆነብኝ ፈተና፣

የየእለቱ ሰቃይ ተደማምሮ በእኔ ላይ፣

ዘጠኝ ወር በሙሉ እንዲሁ ስሠቃይ፣

ደግሞ ደርሳ መጣ ምጥ የሚሉት ጉዳይ፡፡

ግዴታ ነውና እንደወጉ ጫካ ውስጥ መገላገል፣

ከቤቴ ውስጥ ወጣሁ ልጄን ልገላገል፣

ኡ ኡ ኡ ኡ ይሰማ ህመሜ!

ኡ ኡ ኡ ኡ ይሰማ ህመሜ!

በደል ዶርሶብኛል በልጅነት ዕድሜ፣

ልጅ አልወጣ ብሎኝ ሰባት ቀን ሙሉ አማጥኩኝ፣

ስቃየኝ ላውራችሁ ገና መቼ ጨረስኩኝ፤

ሣምንት ሙሉ አምጬ በተገላገልኩ፣

ድካም በዝቶብኝ ትንሽ አርፍ አልኩኝ፣

ቡዙም አልቆየሁም ነቃሁ ልጸዳዳ፣

ያለሁ ብቻዬን ሁሉም በየጎዳ፣

ልጄን ባገላብጥ ትንፋቹ አጣሁኝ፣

ሙት ልጅ መውለዴን አሁን ተረዳሁኝ፡፡

እረ አለገና በኔ የደረሠ፣

መቆጣጠር አቅቶኝ ሽንቴ እየፈሰሠ፣

የሚፈሰው ሁሉ ሽታው ጠነከረብኝ፣

ከሰው መቀላቀል በጣም አስቸገረኝ፡፡

ከቤትም ከውጭም መገለሉ መጣ፣

ባለቤቴም ጣላኝ ባልፈጠርኩት ጣጣ፣

ችግሬን ሁሉ ተቀብዬ በተቀመጥኩት፣

ደግሞ ሌላ ችግር ጣጣ መጣ ሸኘት ወደ ቤት፣

በእኔ ምትክ ትንሽ እህቴ በጋብቻ ልትቀየር፣

ጎጀዬ ሊፈርስ ባልሰራሁት ኃጢያት፣

የጠላኝ ባለቤቴ ሽማግሌ ልኮ፣

እህቴ ለመውሰድ ጉድ አደረገኝ እኮ፣

ቤተሰቦቼም ተወሰነባቸው እህቴን ሊሰጡ፣

ምን ምርጫ አላቸው ወዴትስ ሊያመልጡ፡፡

ህጉ ቢደነገግ በተግባር ካልዋለ፣

በደላችን አይቆምም ትውልድ ተበደለ፣

እኔማ እምፈለወገው ጤናዬን የሚጠብቅልኝ፣

ሠርዓትና ህግ በመንደሬ የሚተገብርልኝ ምነው ቢመጣልኝ፣

በቤትም በውጭ የስራ ጫና በዝቶ፣

ሥራ ተደራርቦ ለሴቶች እንደ እርግማን በዝቶ፣

እረ ምን ይባላል ይህ ጉድ በዝቶ፡፡

በህብረተሰቡ ውስጥ ገብቶ ታግሎ የሚታግልን፣

ረዳት አጋር የሚሆነን ወገን አሰፈለገን፣

በኔ ላይ ይቅር ጎጂ ልማዳዊ ዲርጊት ይጥፋ፣

ትውልድ ነጻ ይውጣ ትምህርት ቤት ይስፋፋ፣

ትምህርት ቤት መሰረት ነው ለሠው ልጆች እድገት፣

ይሰጠኝ እድሉ እኔም ልማርበት፣

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሆኑትን እናውግዝ በይፋ፣

ብርሃን ይብራልን ትምህርት ቤት ይስፋፋ፣

ስለዚህ ጥሪየት ለትውልድ እንዲተርፍ፣

ወገኖቼ እርዱኝ እፎይ እፎይ ቢዬ ልረፍ፡፡

በትርሀስ መዝገበ